# በኢትዮጵያ፡ የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅርንጫፍ በኾነችው፡ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አዘጋጅነትና አቅራቢነት፡ በኢትዮጵያ፡ የዓለም አቀፉ ፀረ-ማርያም ድርጅት ቅርንጫፍ የኾነው፡ የመጽሓፍ ቅዱስ ማኅበር አሳትሞ ስላሠራጨው፡ ስለዕሥራ ምዕቱ መጽሓፍ ቅዱስ፡

## የተላለፈ ግልጽ ደብዳቤ።

**ይድረስ፡-** ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፤
በያላችሁበት።

**የተላከ፡-** ከንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፤
የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ።

በብፁዕ ዕጨጌ ጳውሎስ፥ "የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ሊቀ መንበር" ፈቃድና ትእዛዝ፡ በቤተ ክህነቱ ሊቃውንት ጉባኤ፡ በኢትዮጵያኛ ተዘጋጅቶ፡ በዕሥራ ምዕቱ መባቻ፡ በ"ኢትዮጵያ መጽሓፍ ቅዱስ ማኅበር" ታትሞ የወጣው፥ የብሉያትና የሓዲሳት መጻሕፍትን የያዘው መጽሓፍ ቅዱስ፡ በቅርቡ ደርሶኝ አየሁት።

ወደውስጥ ገብቼ፡ ገና ዝርዝሩን ባልመለከተውም፡ በአንድ በኩል፡ በመቅድሙና በመግቢያው በተገለጹት አሳቦች፥ እንዲሁም፡ ገጾቹን፡ በአጠቃላይ አገላብጬ ስቃኝ፡ ቤተ ክህነቱ ጭምር ትቶት የነበረው፡ መላው የአኀዛት አጻጻፍ፡ የግእዙን ሥርዓት እንዲከተል መደረጉን በማስተዋሌ፡ ደስ አለኝ። በሌላ በኩል ደግሞ፡ የቅዱሱ ኪዳኗ ኢትዮጵያችንን፡ እውነተኛ ማንነትና ቀዳማዊ ጥንታዊነት፥ ሕያው ይዞታና ኪዳናዊ ውርስ የሚፈታተኑ፡ አንዳንድ የፀረ-ኢትዮጵያ ድርጊት ምልክቶችን ስላገኘሁበት፡ ቅርታ ተሰማኝ።

ከዚህ የተነሣ፡ በምንም መልኩና ይዘቱ፡ ሊገሠሥ የማይቻለው፡ የዚችው የእናት ሃይማኖታችንና አገራችን ህልውና ተጠብቆ የመቀጠሉን እውነታ የማረጋገጡ አደራና ኃላፊነት፡ የእኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቿ፡ መሠረታዊ አቋማችንና ዓላማችን በመኾኑ፡ በዚህ ረገድ፡ ከእኛ የሚጠበቀውን፡ የአገልግሎታችንን ገንቢ አስተያየትና ትችት በማከል፡ ይህን፡ ቀዳሚ ግልጽ ደብዳቤ ልጽፍላችሁ ወደድሁ።

ደስ ያለኝ፡ ከላይ፡ ባጭር በጠቀስሁት ምክንያት ብቻ አልነበረም። ሌላ፡ ተጨማሪ ምክንያትም ነበረኝ፤ ይኸውም፡ ራሴ፡ በግልም ኾነ፡ በተጣለብኝ ኃላፊነት፡ ልፈጽመው፡ ለረዥም ዘመን እጥርበት የነበረው አንዱ ኢትዮጵያዊ ግዳጄ፡ ምናልባት፡ የመጨረሻው ባይኾንም፡ ከአንዳች ግብ የደረሰ ስለመሰለኝ ነበር፡ ደስ ተሰኝቼ የነበርሁት። ያም የኢትዮጵያዊነቴ ግዳጅ፡ ግእዙን መሠረትና ምስክር ያደረገ፡ የተሟላውን ኢትዮጵያዊ የቅዱሳት መጻሕፍት ነጠላ ትርጓሜ ማዘጋጀት ነው።

ይኸን ዝግጅት፡ በውጥንነት የጀመርሁት፡ ገና፡ በኢትዮጵያ ድርሰት ማኅበር መሥራችነትና ዋና ጸሓፊነት፥ በአኵስም ጽዮን ንቡረ እድነትና ቀደም ባሉት በቤተ ክህነት የየክፍል መሪነት፥ በመጨረሻም፡ በዚሁ፡ በቤተ ክህነቱ ጠቅላይ ሥራ አስኪያሃጅነት አገልግሎቶች ላይ በነበርሁባቸው ጊዜያት ነበር፤ ያን ተከትሎ በደረሰው፡ በደርግ እሥር ቤት ባሳለፍኋቸው፡ በሰባቱ ዓመታት እንኳ ሳይቋረጥ፥ ከዚያ፡ የይሞት-በቃ ፍርድ፡ በእግዚአብሔር ቸርነት ተርፌ እንደወጣሁም፡ በአገር ቤት፡ በውል ከተቀበልሁት፡ የመጽሓፍ ቅዱስ ትርጉም ሥራዬ ጋር በማያያዝ፡ ይህንኑ ዝግጅቴን ቀጠልሁበት፤ ኋላም፡ በእርሱ ምክንያት፡ በገዛ ፈቃዴ፡ ወደስደቱ ዓለም እንደገባሁ፡ ከአሜሪካው Ford Foundation (ፎርድ ፋውንዴሽን) ጋር በመተባበርና "የኢትዮጵያ ቅዱስ ኪዳን ቅርስ ተቅዋም" በሚል ስያሜ፡ በሕግ አቋቁመነው በነበረው ማኅበር አማካይነት፡ ሳካኺደው ቆየሁ፤ በመካከሉ ግን፡ ይህ መተባበር፡ ለጊዜው፡ በፀረ-ኢትዮጵያ ኃይላት ቢገታም፡ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ኃይል እየተጠናከረ ባደገውና እስከዛሬ በሠመረው፡ በኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎቴ፡ የሕያውነት ህልውናው፡ እነሆ፡ ሊረጋገጥ ቻለ። ስለዚህ ጭምር ነበር፡ ይህን አዲስ መጽሓፍ ቅዱስ አይቼ ስመለከተው፡ ደስ ተሰኝቼ የነበርሁት።

ዕጨጌ ጳውሎስና እኔ፡ "በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ ማንነታችንና ሃይማኖታዊ አስተሳሰባችን አንድ ነን!" ብዬ በማስብበት፡ በዚያ፡ በደርግ ዘመን፡ እርሳቸው፡ በመንግሥት ፈቃድ፡ ከአገር ወጥተው፡ ለዛሬው አገልግሎታቸው፡ይሠለጥኑበት ወደነበረው፡ ወደኒው ዮርክ ከተማ ኼጄ፡ በቃል ካነጋገርኋቸው፡ አያሌ ቁምነገሮች መካከል፡ አንዱ፡ ይህ፡ አኹን ደስ ተሰኝቼበት የነበረው፡ ግእዙን መሠረት ያደረገው፡ የቅዱሳት መጻሕፍት ነጠላ ትርጉም ጉዳይ፡ እንደነበረ አስታውሳለሁ።

ዕጨጌው፡ በዚሁ መጽሓፍ ቅዱስ፡ መቅድማዊ ጽሑፋቸው፡ *"ምናልባት፡ ከግእዙና ከአማርኛው ምንባብ ያመለጡ ቃላት ቢገኙ፡ የመጽሓፍ ኅትመት፡ በአንድ ጊዜ፡ ፍጹም ሊኾን ስለማይችል፡ ከአንባብያን የሚቀርብልንን አሰባስበን፡ በሚቀጥለው ኅትመት እንዲታተም ይደረጋል።"* ብለው ባሳሰቡት መሠረት፡ በዚህ፡ ግልጽ ደብዳቤዬ ላይ እጠቅሳቸው ዘንድ፡ ለጊዜው፡ በአሰሳ መልክ፡ በቅርብ ያገኘኋቸውን ጉድለቶች፡ ከቀላሎቹ በመነሣትና ወደከባዶቹ በማምራት፡ በቅደም ተከትል፡ ከአስተያየትና ትች ጋር፡ እንደሚከተለው፡ ባጭር አቅርቤያቸዋለሁ፡-

፩ኛ. አታሚው የመጽሓፍ ቅዱስ ማኅበር፡ "የፖ. ሣ. ቍጥር 1252" ብሎ የሰጠውን የደብዳቤ አድራሻ፡ ከሥሩ ለሚነበበው ለእንግሊዝኛው አጻጻፍ በመተው፡ "መልእ. ሣ. ቁ. ፩ሺ፪፻፶፪" በሚለው ኢትዮጵያዊ አጻጻፍ ሊያስተካክለው እንደሚገባ ማሳሰቡ ያስፈልጋል።

፪ኛ. በመጽሓፉ የውስጥ ዋና ገበታ፥ እንደገና ደግሞ፡ በመቅድሙ መጨረሻ ላይ በተደረደረው፡ በዕጨጌ ጳውሎስ ረዥም የማዕርጋት ዝርዝር ውስጥ፡ Papas *"ጳጳስ"*፥ Patriarch *"ፓትሪያርክ"* የሚሉት ባዕዳን ቃላት፡ ፈቱኑም ቢኾን፡ "ሊቀ ካህናት"፡ ወይም፡ "ንቡረ እድ"፥ "ዕጨጌ"፥ ወይም፡ "ርእሰ ሊቃነ ካህናት" በሚሉት፡ ኢትዮጵያውያት የግእዝ ቃላት ሊነገሩና ሊጻፉ ይገባ ነበር፤ ነገር ግን፡ ያ ሳይኾን ቀርቶ፡ አኹን እየጸና እንዲኼድ የተደረገው አጠራር፡ እነዚህን ነባሮቹን ኢትዮጵያውያን የማዕርግ ስሞች ለውጦ፡ በባዕዱ ለመተካት የሚፈጸም ሙከራ መኾኑ ግልጽ ነው።

"Patriarch" የሚለው ባዕዱ ቃል፡ እዚያው ዝርዝሩ ውስጥ ተያይዞ፡"ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት" በሚለው ኢትዮጵያኛው ቃል ስለተተረጐመ፡ እንደገና "ፓትሪያርክ" ብሎ መደረቱ አስፈላጊ አልነበረም። እርሱም ቢኾን፡ "ርእሰ ሊቃነ ካህናት" በሚለው ትክክለኛ ትርጉም ተቃንቶ፡ ሊበቃ በቻለ ነበር።

የዘመኑ፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ሊቀ መንበር፡ "ርእሰ ሊቃነ ካህናት" ጳውሎስ፡ የዕጨጌውን የማዕርግ ስም አክለው እንደያዙት ኹሉ፡ የንቡረ እዱንም ለመጠቅለል ከፈለጉ፡ "ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም" በማለት ፈንታ፡ "ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት" እንደተባሉበት ኹሉ፡ "ንቡረ እድ ዘአኵስም" ቢባሉበት በተገባ ነበር። በዚህ ረቂቅ ስልት፡ "ንቡረ እድ" የሚለውን፡ <u>የአኵስም መታወቂያና መለያ የኾነውን፡ ጥንታዊና ታሪካዊ ማዕርግ፡</u> ደብዛው እንኳ እንዳይኖር፡ ስሙን ጭምር፡ እንዲህ አድርጎ ለመደምሰስ መሞከሩ፡ ትልቅ ጥፋት ነው።

ከአጼው በቀር፡ የበላይ አለቃ የሌለው፡ ይህ፡ የንቡረ እዱ መንበርና ማዕርግ፡ ክብሩና መብቱ፡ በባዕዳን አገልጋዮች፡ እንዲህ ሲመዘበር ሲያዩ፡ እኒያ አኵስሞች፡ ለመኾኑ፡ ምን ብለው ይኾን?

ይህ ኹሉ የጥቃት ሥራ፡ በገሃድና በማናለብኝነት፡ እየተካኼደና እየኾነ ያለው፡ እንደዛሬው ጊዜ ኹሉ፡ የበላይና የበታችነትን ደረጃ ለማንጸባረቅና ለማጽናት፥ የገዢና የተገዢነትንም ሰንሰለት ለማሳመንና ለማስቀበል፡ ፀረ ኢትዮጵያ የኾኑት ባዕዳን፡ ለየራሳቸው ጊዜያዊ ሥልጣንና ጥቅም ሲሉ፡ ማንነታቸውን በገንዘብ ከሸጡና ከለወጡ፥ ያገር ፍቅር ከሌላቸውና እምነተ ቢስ ከኾኑ ወገኖች ጋር፡ ኾነ ብለው በመመሣጠር፡ ሲፈጽሙት የኖሩትን ደባ፡ ዛሬም በድፍረት እንደቀጠሉበት ማስተዋል ይገባል።

በዓለም አቀፉ ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይላት ተቋቁሞ የሚሠራው፡ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት፡ ለተጠሪው፡ ለዕጨጌ ጳውሎስ የሰጣቸው፡ "President" የሚለው፡ የማዕርግ ቃል፥ እንዲሁም፡ በመግቢያው ጽሑፍ ውስጥ፡ አዘጋጁ የሊቃውንት ጉባኤ፡ ለዚህ ቋሚ የሃይማኖት መጽሓፍ ተገቢ የኾኑ፡ ብቁ ኢትዮጵያኛ ቃላትን ያጣ ይመስል፡ "budget"፥ "expert" እና "computer" ብሎ፡ ያለመልካቸውና አለቦታቸው ያስገባቸው የወል ቃላት፡ እንደባዕድነታቸው፡ ለእነዚያው ለባዕዳኑ ሆህያትና ሥነ ጽሕፈት ተትተው፡ በእኛው፡ በኢትዮጵያኛው ቋንቋ፡ "ሊቀ መንበር"፥ "የገንዘብ ድልድል"፥ "ባለሙያ" እና "መቀመሪያ" ሊባሉ፡ ይገባል።

፫ኛ. የጥቅሶቹ አኀዞች፡ እጅግ ረቂቃን ከመኾናቸው የተነሣ፡ እነዚህኑ ቊጥሮች ለይተውና አጥርተው ለመመልከት፡ ለብዙዎች አንባቢዎች ስለሚያዳግታቸው፡ እንደሌሎቹ ኹሉ፡ ከፍ ያለ የመሥፈርት መጠን ባላቸው አኀዞች፡ ተተክተው እንዲኀሉ ቢደረግ፡ መልካም ይኾናል።

፬ኛ. ይህ፡ የአዲሱ መጽሓፍ ቅዱስ ዝግጅት፡ በዋናነት፡ መሠረት ያደረገው፡ የግእዙን ዘርዕ መኾኑን፡ በዕጨጌው መቅድምና በአዘጋጁ ሊቃውንት ጉባኤ መግቢያ፡ በአጽንዖት ስለተረጋገጠ፡ ይህንኑ ማረጋገጫ ለማስተማመን፡ ለዓይነት ያህል፡ ከብዙዎቹ መካከል፡ ጥርጣሬው ወደነበረብኝ፡ ወደአንዱ፡ የብሉዩ ኪዳን ክፍል ወደኾነው፡ ወደትንቢተ አሞጽ፡ ምዕራፍ ፱፥ ቊጥር ፯ ገልጬ አየሁ፤ እዚያም፡ የዚሁ ማረጋገጫ አባባል፡ እውነትና ትክክል ሳይኾን ቀርቶ አገኘሁት።

ስለዚህ፡ ይህ ጥቅስ፡ ቀዳማውያኑና እውነተኞቹ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት፡ አብነቱና ዓይነታው ከኾነው፡ ከግእዙ ዘርዕ፡ በቀጥታ ወስደው፡ **"ስሙ፡ ኹሉን የሚገዛ እግዚአብሔር፡ 'የእስራኤል ልጆች! እናንተ፡ በእኔ ዘንድ፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁም፤' አለ፤ 'እስራኤል! ቀድሞ፡ ከከለዳውያን፥ ከሶርያ፥ ከግብፅና ከፍልስጥኤማውያን፡ ያወጣኋችሁ አይደለሁምን?'"** ብለው በተረጐሙት ቃል ተስተካክሎ ሊጸና ይገባል።

፭ኛ. የዚሁ፡ የአዲሱ መጽሓፍ ቅዱስ ቃለ እግዚአብሔር፡ በኢትዮጵያኛው ባህልና ጥሬት ተተርጉሞ እንደኾነ ለማረጋገጥ፡ ከዚህ በማስከተል፡ እንደገና፡ ለዓይነት ያህል፡ አገላብጬ ያየሁት፡ ሌላው ጥቅስ፡ በአዲስ ኪዳኑ ክፍል፡ በብሥራተ ዮሓንስ፡ በምዕራፍ ፲፱፥ ቊጥር ፳፭-፳፯ ውስጥ፡ "ብእሲቶ" የሚለውን ቃል የሚመለከተውን ነው። ዳሩ ግን፡ እዚህም ላይ ያነበብሁት ትርጉም፡ ላየው ጓጕቼ የነበረው እውነተኛው ሳይኾን፡ የእርሱ ተቃራኒው፡ ሓሳዊው ኾኖ አገኘሁት።

ስለዚህ፡ እንደላይኛው፡ እንደብሉይ ኪዳኑ ጥቅስ ኹሉ፡ ይኸኛውም፡ የአዲስ ኪዳኑ ጥቅስ፥ በተለይ፡ በዚያው ምዕራፍ፡ ቊጥር ፳፯ ላይ፡ "አንቺ ሆይ!" ተብሎ የተተረጐመው ቃል፡ "እናቴ ሆይ!" በሚለው፡ ትክክለኛ ቃል ሊተካ የሚገባ ነው።

## ሓተታ

ለመግቢያ ያህል፡ ከላይ፡ በጥቂቱ ያወሳኋቸውን ፍሬ ነገሮች ከገለጽሁ፡ አኹን ደግሞ፡ ከእነዚሁ ፍሬ ነገሮች መካከል፡ በመጨረሻዎቹ፡ ፬ኛና ፭ኛ ተራ ቊጥሮች ላይ፡ ከብሉይ ኪዳኑ አንድ፥ ከአዲስ ኪዳኑም፡ እንዲሁ አንድ፡ ለዓይነት ስለቀረቡት እውነታዎች፡ ከዚህ የሚከተሉትን አጫጭር ሓተታዎች እሰጥ ዘንድ፡ የተጠመድሁበት ተልእኮዬ አስገድዶኛል።

፩ኛ. በቀዳሚነት፡ የብሉይ ኪዳኑን፡ ትንቢተ አሞጽ፡ ምዕራፍ ፱፥ ቊጥር ፯ ጥቅስ ይመለከቷል፤ እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት የተቀበልነው፡ ቀዳማውያኑና እውነተኞቹ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ያስተላለፉልንን፡ እንዲህ የሚለውን፡ የግእዙን የአብነት ቃል ነው፡- "**'አኮ ከመ ደቂቀ ኢትዮጵያ፡ አንትሙ በኀቤየ፡ ደቂቀ እስራኤል!' ይቤ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ ይመልክ ስሙ። 'አኮኑ፡ እስራኤል፡ ዘአውጻእክዎ፡ እምከላውዴዎን? ወእምካራን? ወእምግብፅ? ወእምኢሎፍሊ?'**"

የዚህ የግእዙ ጥቅስ ትርጓሜ፡ የሚከተለው ነው፡- "**ስሙ፡ ኹሉን የሚገዛ እግዚአብሔር፡ 'የእስራኤል ልጆች! እናንተ፡ በእኔ ዘንድ፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁም፤' አለ፤ 'እስራኤል! ቀድሞ፡ [አያታችሁ አብርሃምን፡] ከከለዳውያን፥ [አባታችሁ ያዕቆብን፡] ከሶርያ፥ [እናንተን፡] ከግብፅ፥ [ንጉሣችሁ፡ ዳዊትንም፡] ከፍልስጥኤማውያን፡ ያወጣሁ አይደለሁምን?'**"

ከዚህ ትርጓሜ ጋር የተጠቀሰው፡ የአዲስ ኪዳኑ ምሥራች መጽሓፍ ቃል፡ ማቴ. ምዕ. ፫፥ ቊ. ፱ ሲኾን፡ እርሱም፡ የግእዙን ቃል ትክክለኛነት በማረጋገጥ፡ እንዲህ ይላል፡- "**መጥምቁ ዮሓንስ... ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን ወገን፡ ወደጥምቀቱ ሲመጡ፡ ብዙ ሰዎችን ባየ ጊዜ፡ 'እናንት የእፉኝት ልጆች! ከሚመጣው ቊጣ ትሸሹ ዘንድ፡ ማን አመለከታችሁ? እንግዴህ፡ ለንስሓ የሚያበቃችሁን፡ በጎ ሥራን ሥሩ! አብርሃም አባት አለን በማለት፡ የምታመልጡ አይምሰላችሁ! እግዚአብሔር፡ ከእነዚህ ድንጋዮች፡ ለአብርሃም፡ ልጆችን ማስነሣት እንዲቻለው እነግራችኋለሁ። እነሆ፡ ምሳር፡ በዛፎች ግንድ ላይ ሊወድቅ፡ ተቃጥቷልና፤ መልካም ፍሬን የማያፈራ ዛፍ ኹሉ ይቆረጣል፤ ወደእሳትም፡ ይጣላል።'**"

በትንቢተ አሞጽ፡ ምዕ. ፱፥ ቊ. ፯ ላይ የተጻፈው፡ የአዲሱ መጽሓፍ ቅዱስ ትርጉም ግን፡ እርሱን እንደመሰሉት ትርጉሞች ኹሉ፡ እንዲህ ይላል፡- ***"'የእስራኤል ልጆች ሆይ! እናንተ፡ ለእኔ፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን?' ይላል እግዚአብሔር። 'እስራኤልን፡ ከግብፅ ምድር፥ ፍልስጥኤማውያንንም፡ ከቀጰዶቅያ፥ ሶርያውያንንም፡ ከጉድጓድ፥ ያወጣሁ አይደለምን?'"***

በእኛ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋዮች ዘንድ፡ ተቀባይነት ያለው፡ "አኮ!" በሚለው፡ በመጀመሪያው፡ የግእዙ ዘርዕና "አይደላችሁም!" በሚለው፡ በዚሁ ቃል ትርጉም፡ እግዚአብሔር፡ ለእስራኤል የሰጠው ቍርጥና ግልጽ የኾነው አሉታዊው ምላሹ ነው። "አኮኑ?" ማለትም፡ "አይደላችሁምን?" በሚል መልክ የቀረበው ቃለ መጠይቅ ግን፡ በኹለተኛው ዐረፍተ ነገር ውስጥ በሚነበበው፡ "አኮ" በሚለው ቃል ላይ ከተጨመረው ትእምርተ ጥያቄ የተነሣ የተነገረው ነው።

ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ እስካኹን፡ የእግዚአብሔር የኾነውን ቃልና ሥራ ኹሉ፡ ለምሳሌ፡ ነቢዩ ሙሴንና መሢሕ ኢየሱስን፡ ማንነታቸውንና መልእክታቸውን፡ በሙሉ ፈቃደኛነትና ታማኝነት ተቀብለው ምግባራዊ ካደረጉት፡ ከኢትዮጵያ ልጆች እምነትና ምግባር አንጻር፡ እኒሁ የእስራኤል ልጆች፡ በፈጸሙት ተቃውሞና በደል፥ እንዲያውም፡ ዛሬም፡ በዚያው ዓመፀኝነታቸው ጸንተው፡ እያካኼዱት ባለው ተመሳሳይ ግብራቸው፡ የዚህ፡ የነቢዩ፡ የአሞጽ ቃል፡ እውነተኛነትና ትክክለኛነት፡ ለመላው የምድር ሠራዊትና ለሰማይ መላእክት፡ ለአንዴና ለዘለዓለሙ ተረጋግጧል። ያም ግብራቸው፡ አብርሃም፡ በኢትዮጵያዊው መልከ ጼዴቅ ትምህርት፡ ከጣዖት አምልኮ፡ ወደሃይማኖተ እግዚአብሔርና ወደኪዳነ ግዝረቱ ሕይወት ከገባ በኋላ፡ ከእርሱ ዘር የተገኙት፡ እኒሁ የእስራኤል ልጆች፡ ቀድሞ፡ በብሉዩ ዘመን፡ ከሊቀ ነቢያት ሙሴ ጀምሮ፡ እስከተፍጻሜተ ነቢያት (የነቢያት መደምደሚያ እስከኾነው) መጥምቁ ዮሓንስ ድረስ በነበሩት፡ በቅዱሱ ኪዳን ልኡካን ላይ፥ በመጨረሻ፡ በአዲስ ኪዳኑ ዘመን ደግሞ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ በሰውነት ተወልዶ፡ በዚህ ዓለም በተገለጠው፡ በራሱ፡ በእግዚአብሔር ልጅ ላይ፡ በአንገተ-ደንዳናነታቸው ያደረሱት የግፍ ኃጢአት ነው።

ከማንኛውም የዓለም ሕዝብ በፊት፥ የቀደሙትና የተወደዱት እውነተኞቹ የእግዚአብሔር ልጆች፡ ኢትዮጵያውያን መኾናቸው ተረጋግጦ፡ በትንቢተ አሞጽ ከተነገረው፡ ከዚያ መለኮታዊ ቃል አንጻር፡ እስራኤላውያን፡ የእግዚአብሔር ቀንደኛ ተቃዋሚ የኾነው፡ የሓሰተኛው መንፈስ ልጆች መኾናቸው፡ ያውም፡ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንደበት የተነገረባቸው በመኾኑ፡ የዚሁ፡ የነቢዩ ቃል እውነተኛነትና ትክክለኛነት፡ በበለጠ ተረጋግጦ ጸንቷል፤ ይህም፡ *"አባታችን አብርሃም ነው!"* ደግሞም፡ *"አንድ አባት አለን፤ እርሱም፡ እግዚአብሔር ነው!"* ላሉት፡ ለእስራኤላውያኑ አይሁድ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "የለም! አይደላችሁም!" በሚል ቍርጥ ውሳኔ፡ "እናንተ፡ ከአባታችሁ፡ ከዲያብሎስ ናችሁ፤ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወድዳላችሁ፤ እርሱ፡ ከመጀመሪያ፡ ነፍሰ ገዳይ ነበር፤ እውነትም፡ በእርሱ ስለሌለ፡ በእውነት አልቆመም። ሓሰትን ሲናገር፡ ከራሱ ይናገራል፤ ሓሰተኛ፥ የሓሰትም አባት ነውና።" ሲል ባስሰማው አምላካዊ ቃሉ፡ የተገለጸው የእውነቱ ምስጢር ነው። (ዮሓ. ፰፥ ፴፱-፵፬።)

ታዲያ! በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ ተቀባይነት ባለው፡ በግእዙ ዘርዕ፡ "አኮ!"፥ በኢትዮጵያኛውም ትርጉም፡ "አይደላችሁም።" የሚለው፡ ቍርጥና ግልጽ የኾነው፡ የእግዚአብሔር አሉታዊ የውሳኔ ቃል፡ በአዲሱ መጽሐፍ ቅዱስ፡ "አኮኑ?"፥ በኢትዮጵያኛውም ትርጉም፡ "አይደላችሁምን?" ተብሎ፡ ወደቃለ መጠይቅነት የተለወጠው፡ ለምንድር ነው? እነማንን ለመደገፍ፥ ወይም፡ ለማስደሰት ነው? ይህ ከባድ ለውጥ ሲደረግስ፡ እንደሌሎቹ፡ መሰል፥ ወይም፡ የተለዩ ኾነው ለተገኙት፡ ለባዕዳኑ ቃላት ሳይቀር፡ በጎዳግ፥ ወይም፡ በግርጌ፡ የመጠቀስ ዕድል እንደተሰጣቸው ኹሉ፡ ይኸው ቃል፡ መኖሩ እንኳ፡ ለምን ሳይገለጽ ቀረ?

፫ኛ. በተከታይነት ደግሞ፡ በአዲስ ኪዳኑ ክፍል፡ በብሥራተ ዮሓንስ፡ በምዕራፍ ፲፱፥ ቍጥር ፳፭-፳፯ ውስጥ፡ "ብእሲት" የሚለውን ሌላውን ጥቅስ ይመለከቷል።

ይኸውም፡ ከሌሎቹ፡ ከዘጠኙ ትእዛዛቱ ጋር፡ "አባትህንና እናትህን አክብር!" ብሎ፡ ገና በፍጥረት ልደት ጊዜ፡ በመልኩ በፈጠረው፡ በሰው ሕሊና ላይ፡ በኪዳነ ልቦና የጻፈውንና በመካከለኛው ዘመነ ኦሪት፡ በጽላት ላይ ቀርፆ የሰጠውን ቃል ኪዳን፡ ይኸው ፍጡሩ፡ ለመፈጸም ፈቃደኛ ካለመኾኑና ካለመቻሉ የተነሣ፡ ስለጠፋ፡ በፍጻሜው ዘመን፡ በራሱ መሥዋዕትነት ሊያድነውና በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ፡ የዘለዓለም ምሕረትን ሊያቀዳጀው፡ ሰው ኾኖ የመጣው ፈጣሪ፡ የቤዛነቱን፡ የመጨረሻ ጽዋ በጨለጠበት መስቀሉ ላይ ያስሰማውን፡ እውነተኛ መለኮታዊ የኑዛዜ ቃል የሚያፈርሰውን፡ ሓሳዊ የፍጡር አነጋገር የሚያመለክተው ነው።

ያ ሓሳዊ የፍጡር አነጋገር፡ "የሰማይና የምድር ፈጣሪ፡ እግዚአብሔር አምላክ የኾነው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እናቱን፡ ቅድስት ድንግል ማርያምን የተሰናበታት፡ 'አንቺ ሆይ!' በሚል አጠራር ነው!" ብለው የዛሬዎቹ፡ የዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ዝግጅት ሊቃውንት ጉባኤ ያቀረቡት፥ ዕጨጌ ጳውሎስም ያጸደቁት አተረጓጎም ነው። ይህም አተረጓጎም፡ "የለም! የጠራት፡ 'ሴትዮ!' ብሎ ነው!" ብለው ከተረጎሙት፡ ከቀደሙት የቤተ ክህነቱ የሊቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢና አባሎች ግብር፡ ምናልባት፡ ጥቂት የተሻለ መስሎ ይታይ ይኾናል እንጂ፡ ከዚያ "የተለየ ነው!" ተብሎ ከቶ የሚታሰብ አይደለም።

ይህንም ስል፡ እጅግ አጠያያቂና አሳሳቢ ስለኾነው፡ ስለዚሁ ርእሰ ነገር፡ ቀደም ብለው በወጡት መጻሕፍቴና በየአጋጣሚው፡ በጎዋ ሰሌዳችን ላይ በወጡት መልእክቶች አማካይነት፡ ደጋግሜና አበክሬ የሠነዘርሁት ግልጽ ትችና የሰጠሁት ገንቢ አስተያየት፡ በቤተ ክህነቱ ዘንድ፡ ከጕዳይ ተቆጥሮ፡ ከግምት ውስጥ እንዳልገባና የጥፋቱ ድርጊት ኾን ተብሎ፡ እንዲቀጥል መደረጉን፡ በትዝብት በመመልከት ነው።

ይኸው፡ አዲሱ መጽሓፍ ቅዱስ ኾነ፡ ሌላውም ኹሉ፡ ቅድስት ድንግል ማርያምን፡ "እናቱ" እያለ በመደጋገም የሚጠቅሳት መኾኑን፥ ራሱ ልጇ፡ ኢየሱስ ክርስቶስም፡ እርሷን፡ ለደቀ መዝሙሩ፡ ለዮሓንስ፡ በአደራ የሰጣት፡ "'እናትህ እነኋት!' ብሎ እንደኾነ፥ እርሱን፡ ራሱን፡ ደቀ መዝሙሩንም፡ ለእናቱ አደራ ሲሰጣት፡ 'እነሆ ልጅሽ!' ብሎ እንደኾነ፡ እኒሁ፡ የቤተ ክህነት ሊቃውንት፡ ተምረውት የሚያስተምሩት፥ በትርጉማቸውም፡ የጻፉት ግልጽ እውነታ ነው።

እንዲህ ከኾነ፡ ታዲያ! ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በትስብእትነቱ የወለደችውን፡ እርሷን፡ እናቱን፡ ድንግል ማርያምን የጠራት፡ "'እናቴ ሆይ!' በማለት ፋንታ፡ 'አንቺ ሆይ!'፥ እንዲያውም፡ 'ሴትዮ!' ብሎ ነው!" ማለት፡ ለምን ይኾን? የክፋት መንፈስ፥ ወይም፡ አኹንም፡ እንደገና፡ እነዚያኑ፡ "የማርያም ጠላቶች የኾኑ ወገኖችን ለማስደሰትና ለመደገፍ ነው!" ከማለት በስተቀር፡ ሌላ ትችት አይኖረውም።

ምናልባት፡ እኒሁ ሊቃውንት፡ "ግእዙ፡ 'ብእሲቶ' የሚለውን ዘርዕ፡"ሴትዮ!" ብለው የተረጐሙት፡ በድንግል ማርያም ላይ ያደረባቸው ሥውር ሰይጣናዊ ጥላቻ፡ በባሰባቸው ጊዜ ከኾነ፥ ይኸው፡ አባዜያቸው፡ መለስ ሲልላቸውና ሲሻላቸው ደግሞ፡ 'አንቺ ሆይ!' ብለው ተርጉመውት ከኾነ፡ የሚሰሰጣቸው መልስ፡ ከዚህ በሚከተለው ቃል ይጠቃለላል፡-

"ጥፋቱ፡ ከግእዙ ዘርዕ ሳይኾን፡ ከእናንተ፡ ከሊቃውንቱ ስሑት አተረጓጐም የመነጨ መኾኑ ፍጹም ግልጽ ነው! እንዲያ ካልኾነ፡ ታዲያ፡ ለምንድር ነው፡ ጥንቱኑ፡ በኦሪት ዘልደት (ዘፍጥረት)፡ 'ወነደቃ እግዚአብሔር፡ ለይእቲ ዕፅመ ገቦ፡ እንተ ነሥአ እምአዳም፤ ወረሰያ ብእሲተ፤ ወአምጽአ ኀበ አዳም። ወይቤ አዳም ሶቤሃ፡ 'ዛቲ ዕፅም፡ እምዕፅምየ፤ ወሥጋ፡ እምሥጋየ፤ ለትኩነኒ ብእሲትየ! እስመ እምታ ወጽአት ይእቲ።' ወበእንተ ዝንቱ፡ የኀድግ ብእሲ፡ አባሁ፥ ወእሞ፤ ወይተልዋ ለብእሲቱ፤ ወይከውኑ ክልኤሆሙ፡ አሓደ ሥጋ።' ያለው?

"ደግሞም፡ ይኸው ቃል፡ በጥንቶቹ እውነተኞች ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት፥ ዛሬም ባላችሁት፡ በቀደሙትና በአኹኖቹ የቤተ ክህነት ሊቃውንት ሳይቀር፡ 'እግዚአብሔር፡ ይህችን፡ ከአዳም ጐን የነሣትን ዐጥንት፡ ሴት አድርጎ ሠራት፤ ወደአዳምም አመጣት። ያንጊዜም አዳም፡ 'ይህች ዐጥንት፡ ከዐጥንቴ፥ ሥጋዋም፡ ከሥጋዬ ናት፤ እርሷ፡ ከባሏ ተገኝታለችና፡ ሚስቴ ትኹነኝ!' አለ። ስለዚህም ነገር፡ ሰው፡ አባቱንና እናቱን ይተዋል፤ ሚስቱንም ይከተላል፤ ኹለቱም፡ አንድ ሥጋ ይኾናሉ።' ተብሎ፡ ለምን ተተረጐመ?

"'ትኩነኒ ብእሲትየ፤ ወይተልዋ ለብእሲቱ፤' የሚለውን፡ የግእዙን ዘርዕ፡ "ሚስቴ ትኹነኝ! ሚስቱንም ይከተላል፤" ብሎ አሻሽሎና አስተካክሎ፥ አሳምሮም ከመተርጎም ይልቅ፡ 'ወረሰያ ብእሲተ፤' ማለትም፡ 'ሴት አድርጎ ሠራት፤' የሚለውን አተረጓጐም በመከተል፡ ለምን፡ 'ሴቴ ትኹነኝ! ሴቱንም ይከተላል፤' ተብሎ አልተተረጐመም?" (ዘፍ. ፪፥ ፳፪-፳፬።)

ከላይ በተጠቀሰው፡ የእግዚአብሔር ቃልና ትክክለኛ አተረጓጐም መሠረት፡ "ብእሲት"፥ ወይም፡ "ብእሲቶ" የሚለው ቃል "ሴት"፥ ወይም፡ "ሴቱ" ከሚለው ትርጉም አልፎ፡ "ሚስት"፥ ወይም፡ "ሚስቱ"፥ እንዲያውም፡ በዛሬው ዘመን፡ የጨዋና የሠለጠነ አነጋገር ኾኖ፡ "ባልተቤት"፥ ወይም፡ "ባልተቤቱ" ከሚል ደረጃ እንዴት እንደደረሰ፡ ከላይኛው ጥቅስ፡ ቀደም ያለውን፡ እንዲህ የሚለውን፡ የኦሪት ዘልደቱን ቃል፡ በማስተዋል መመልከት ነው።

**"ወይቤ እግዚአብሔር፡ 'ንግበር ሰብአ፡ በአርአያነ፥ ወበአምሳሊነ!"** ማለትም፡ **"እግዚአብሔርም አለ፡ 'ሰውን፡ በመልካችንና በምሳሌአችን እንፍጠር!"** ብሎ በአንድ አካልነት የፈጠረውን ሰው፡ በኋላ፡ ወልደው፡ ይበረክቱ ዘንድ፥ ተዋልደውም ይበዙ ዘንድ፡ በኹለት ጾታነት የሠራቸው መኾኑን፡ **"ወገብሮ እግዚአብሔር፡ ለእጓለ እመሕያው፡ በአምሳለ እግዚአብሔር፡ ተባዕተ፥ ወአንስተ።"**

ማለትም፡ **"እግዚአብሔርም፡ ሰውን፡ በእግዚአብሔር አምሳል ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አደረጋቸው።"** በሚለው ተከታታይ ቃል፡ የእግዚአብሔር መልኩ፡ የወንድ መልክና የሴት መልክ፡ ኹለቱም፡ የእግዚአብሔር መኾኑ ጭምር፡ ተረጋግጧል።

ይህም እውነታ፡ የአምላክ እናት ለመኾን በበቃችው፡ በቅድስት ድንግል ማርያምና ከእርሷ በተወለደው፡ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ገሃድ ኾኗል። (ዘፍጥ. ፩፥ ፳፮-፳፰።)

"ብእሲቶ!" የሚለውን፡ የግእዙን ዘርዕ፡ አላገባብ በመተርጐም፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ቅድስት እናቱን፡ ድንግል ማርያምን፡ "'ሴትዮ!' ነው ያላት፤" ብለው፡ የቀደሙት፡ የቤተ ክህነቱ ሊቃውንት ጉባኤ ባወጡትና የዛሬዎቹም ባጸኑት፡ የአዲስ ኪዳኑ መጽሓፍ ውስጥ ባለው፡ በማቴዎስ ምሥራች፡ ምዕራፍ ፲፱፥ ቁጥር ፫-፲፪፡ እነዚያን፡ ከላይ የተወሱትን፡ የኦሪት ዘልደቱን ጥቅሶች የሚያጠናክር የአተረጓጐም ማረጋገጫን እናገኛለን።

ይኸውም፡ **"ወአውሥአ [እግዚእ ኢየሱስ] ወይቤሎሙ፡- 'ኢያንበብክሙኑ ዘውስተ ኦሪት፡ እግዚአብሔር፡ ከመ ፈጠሮሙ እምትካት፡ ተባዕተ፥ <u>ወአንስተ</u>፤ ብእሴ፥ <u>ወብእሲተ</u> ገብሮሙ?' "** ማለትም፡ **"እርሱ [ጌታችን ኢየሱስ] መልሶ እንዲህ አላቸው፡- 'በኦሪት ያለውን አላነበባችሁምን? እግዚአብሔር፡ ጥንቱን፡ ወንድና <u>ሴት</u> አድርጎ የፈጠራቸውን፡ ባልና <u>ሚስት</u> እንዳደረጋቸው?'"**

በመጨረሻም፡ **"ወይቤልዎ አርዳኢሁ፡ 'እመሰ፡ ከመዝ ውእቱ፡ ሥርዓተ ብእሲ፥ <u>ወብእሲት፡</u> አኮ ሠናይ አውስቦ።"** ማለትም፡ **"ደቀ መዛሙርቱም፡ 'የባልና <u>የሚስት</u> ሥርዓት፡ እንዲህ ከኾነስ፡ ማግባት፡ መልካም አይደለም፤' አሉት።"** የሚለው ነው።

በዚህ ረገድ፡ በእኛዎቹ የቤተ ክህነት ሊቃውንት የተደረገው ጸያፍ አተረጓጐም የሚያሳዝን ሲኾን፡ "ፀረ-ማርያም" በተባሉት፡ በአንዳንድ አክራሪ "ወንጌላውያን ክርስቲያኖች ነን!" በሚሉ ወገኖች ዘንድ ግን፡ በዚሁ ቃል ትርጉም በኩል ተፈጽሞ ያየሁት ድንቅ ነገር፡ ለሥጋውያን ሰዎች፡ እንቆቅልሽ፥ ለሃይማኖታውያንም፡ ተአምር በመኾኑ፡ እዚህ ላይ፡ ላወሳው የሚገባ ይመስለኛል።

የዚህ ድንቅ ነገር ዝርዝር፡ እንዲህ በሚል አጭር ዘገባ ሊጠቃለል ይቻላል፡- ከላይ፡ በዚህ ጽሑፍ መነሻ እንደገለጽሁት፡ እኔ፡ በእግዚአብሔር ቸርነት፡ ከደርግ የሞት ፍርድ ተርፌና ከእሥር ተፈትቼ እንደወጣሁ፡ የአፍሪቃ ክልል መሥሪያ ቤቱ፡ ናይሮቢ፥ ኬንያ የኾነው፡ Living Bibles International (ሊቪንግ ባይብልስ ኢንተርናሽናል) የተባለው፡ ዓለም አቀፍ የመጽሓፍ ቅዱስ ተርጓሚ፥ ዐታሚና አሠራጭ ድርጅት፡ የተርጓሚነት አገልግሎቴን እንዳበረክተው ስለጠየቀኝ፡ የትርጉሙን ሥራ፡ በጽሑፍ ውል ተቀብዬ ጀመርሁ።

ሥራውን የጀመርሁት፡ የምተረጕማቸው ቅዱሳት መጻሕፍት፡ የግእዙን ዘርዕ፡ መሠረትና ምስክር በማድረግ ስለመኾኑ፡ ቀደም ብዬ ያቀረብሁትን የውል ድርድር፡ ድርጅቱ ተስማምቶ ስለተቀበለው ብቻ አልነበረም፤ ከዚሁ ስምምነታችን በፊት፡ በዚሁ ድርጅት፡ ተተርጉሞ ባየሁት፡ በአዲስ ኪዳኑ መጽሓፋቸው ውስጥ፡ ድንግል ማርያምን የሚመለከቱት ጥቅሶች፡ ተገቢው የትርጉም ብቅዓት ተሰጥቷቸው በማግኘቴ ጭምር ነበር፡ ሥራውን፡ በመተማመን ጀምሬ የነበርሁት። ያም ኾኖ፡ ግእዙን አብነት በማድረግ ልተረጕም፡ ከድርጅቱ ጋር፡ በውለታ፡ በተስማማነው መሠረት ለመቀጠል ካልቻልሁበት ደረጃ በመድረሴ፡ ያን፡ የጀመርሁትን፡ የተርጓሚነት ሥራ፡ ብዙም ሳልቆይበት፡ አስረክቤ እንድለየው ተገደድሁ።

በዚሁ ድርጅትና በእኔ መካከል ስለነበረው የትርጉም ሥራ ግንኙነት፡ ይህን ያህል ካዘከርሁ፡ ድንግል ማርያምን በሚመለከት፡ ወደተነሣንበት ርእስ ተመልሰን፡ በተያያዘ መልኩ፡ እነዚያን፡ ከላይ የተወሱትን ጥቅሶች፡ በማስተዋል እያየን እናመዛዝናቸዋለን፤ እነርሱም፡ በብሥራተ ዮሓንስ፡ ምዕ. ፪፥ ቁ. ፬ እና ምዕ. ፲፱፥ ቁ. ፳፮ ላይ የተጻፉት፡ በግእዙ፡ "ኦ ብእሲቶ!' የሚለውን ቃለ ተዋሥኦ (ምላሽ) እና ቃለ ጽዋዔ (አጠራር) የያዙት ናቸው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም፡ ላስሰማት፡ ለእነዚሁ፡ መለኮታውያን፡ የመልስና የጥሪ ቃላቱ፡ የቀደሙትና የዛሬዎቹ የቤተ ክህነት ሊቃውንት፡ የሰጡት ኢትዮጵያኛ ትርጉም፡ ለመጀመሪያው፡ *"አንቺ ሆይ! ካንቺ ምን አለኝ?"* እና *"አንቺ ሆይ! ካንቺ ጋር ምን አለኝ?"*፥ ለኹለተኛውም፡ *"ሴትዮ! እነሆ ልጅሽ!"* እና *"አንቺ ሆይ! እነሆ ልጅሽ!"* የሚል እንደኾነ፡ መጻሕፍቶቻቸው ይመሰክሩባቸዋል።

በዚህ አንጻር ደግሞ፡ ስሙ፡ ከላይ የተጠቀሰው፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ድርጅት፡ በዮሓንስ ምሥራች፡ በምዕ. ፪፥ ቍ. ፬ ላይ፡ ለዚሁ፡ "ብእሲቶ!" ለሚለው ቃለ ተዋሥኦ፡ የሰጠው ኢትዮጵያኛ ትርጉም፡ <u>"እናቴ ሆይ! ታዲያ ምን ላድርግ?"</u> የሚል ሲኾን፥ በዮሓንስ ምሥራች፡ በምዕ. ፲፱፥ ቍ. ፳፮ ላይ ላለው፡ " ኦ ብእሲቶ!" ለሚለው ቃለ ጽዋዔም፡ የሰጠው ኢትዮጵያኛ ትርጉም፡ "ኢየሱስም፡ እናቱን፡ የቅርብ ወዳጁ ከኾነው፡ ደቀ መዝሙር ጋር ቆማ ሲያያት፡ <u>'ካኹን ጀምሮ፡ ልጅሽ፡ እርሱ ነው!'</u> አላት።" በሚል መልክ የተገለጸው ነው።

አዎን! በፀረ ማርያምነት አቋም ጸንተው እያሉ፡ እንዲህ፡ የአፍቃሬ ማርያምነትን ሙያ ሠርቶ መገኘት፡ በሥጋውያኑ ዘንድ፡ "እንቆቅልሽ" ሲኾን፥ በሃይማኖታውያኑ ዘንድ ግን፡ ኃይለ-ማርያም (የማርያም ኃይል) የኾነው መንፈስ ቅዱስ፡ ራሳቸውን፡ ፀረ-ማርያሞቹን፡ ፊታቸውን ጸፍቶና አፋቸውን አስከፍቶ፡ የእግዚአብሔርን እውነት በማናገሩ፡ "ተአምር ነው!" ተብሎ፡ ከላይ፡ እንደድንቅ ነገር ለተቆጠረው፡ ለዚህ ድርጊት፡ ይህን የመሰለው ትችት መሰጠቱ፡ አግባብነት ይኖረዋል።

እንግዴህ፡ ስለተነሣሁበት፡ ስለዚሁ ታላቅ ቍም ነገር፡ ማመዛዘኛ ይኾን ዘንድ፡ ይህን፡ አንድ፡ የእንቆቅልሽ ምሳሌ ከሰጠሁ በኋላ፡ ሓተታዬን፡ ከዚህ በሚከተለው ቃል በማጠቃለል፡ እደመድማለሁ፡-

ዋናው ጥያቄ፡ በግእዙ ዘርዕ፡ "ብእሲት"፥ በኢትዮጵያኛ ትርጉሙም፡ "ሴት" የሚለው አንዱ ቃል፡ "ሚስት" ተብሎ ይተረጐም ዘንድ፡ አግባብ ከኾነና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በመስቀል ላይ ሣለ፡ ቅድስት እናቱን፡ ድንግል ማርያምን፡ በግእዙ "ብእሲቶ" ብሎ ነው የጠራት ከተባለ፡ ታዲያ! <u>ይህንኑ ቃል፡ እንደባህላችን በመተርጐም፡ "እማማ!" ወይም፡ "እናቴ ሆይ!" ብሎ ነው የጠራት ተብሎ፡ ለምን አልተተረጐመም?</u> ለምን፡ "ሴትዮ!" ወይም፡ "አንቺ ሆይ!" ተብሎ፡ በጸያፍ ተተረጐመ? እዚህ ላይ፡ ዋናው ጥያቄ፡ ይህ ነው።

የዚህ ጥያቄ መልስ ግን፡ ግልጽ ነው፤ እርሱም፡ እንዲህ በሚል፡ አጭር ቃል ሊጠቃለል ይቻላል፡-

በአኹኑ ጊዜ፡ በኢትዮጵያም ኾነ፥ በመላው ዓለም ያሉት፡ ቀንደኞቹ መሪዎች ኹሉ፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው መንበሮች ላይ ተንሰራፍተው የተቀመጡት፡ እነርሱ፡ እንደሞኝ ለሚቆጥሩት፡ ለተራው ሰው እንደሚመስለው፡ ለእርሱና ለአገሩ የሚጠቅም፡ ቋሚ ሥራ ለመሥራት አይደለም።

በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ እንደሚታወቀው ደግሞ፡ የሰባት ሺህ አምስት መቶ ሦስት ዓመታት፡ የነጻነት ዕድሜ ያላትንና ዘለዓለማዊት የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችውን፡ ይህችን፡ የቅዱሱ ኪዳኗን ኢትዮጵያ፥ ከእግዚአብሔርና በእግዚአብሔር፥ የእግዚአብሔርና ለእግዚአብሔር የኾነውን ህልውናዋንና ስሟን፥ ክብርዋንና አደራዋን ለመጠበቅም አይደለም።

እርሷም፡ ከልጇ፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በሰማይና በምድር ነግሣና ሰፍና፡ ፍጥረትን፡ በሃይማኖትነትና በአገርነት፥ በእናትነትና በንግሥትነት የምትመግበውና የምትንከባከበው፥ የምትመራውና የምታስተዳድረው፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ናት።

ነገር ግን፡ አዎን! በአኹኑ ጊዜ፡ በኢትዮጵያም ኾነ፥ በመላው ዓለም ያሉት፡ ቀንደኞቹ መሪዎች ኹሉ፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው መንበሮች ላይ ተንሰራፍተው የተቀመጡበት፡ ተቀዳሚ ዓላማቸውና ውሳጣዊ ተልእኳቸው፡ ይህችኑ፡ የቅዱሱ ኪዳኗን ኢትዮጵያ፡ በክፋት መናፍስት እየተገፉ ሊያጠፏት ለሚራወጡት፡ ለወገንና ለባዕዳን ተቃዋሚዎቿ፡ ጥሩ መሣሪያዎችና ታማኝ አገልጋዮች በመኾን፡ ስለእነርሱ ቆሞና ተከላክሎ፡ የጋራ ጥቅማቸውንና ፍላጎታቸውን ለማራመድ ነው።

ይህም እውነታ፡ እነሆ፡ በኹሉም አግጣጫ እየቀጠለና እየተፈጸመ ባለው ግብራቸው፡ ገሃድ ኾኖ ታይቷል፤ እየታየም ነው።

እንዲህ ከኾነ፡ እንግዲያስ፡ በዘለዓለማዊው እመ አምላክነቷና ኪዳነ ምሕረትነቷ፡ መለኮታዊዉን ዕርቅና ሰላም፥ ብልጽግናና ሕይወት፡ ለፍጥረተ ዓለሙ፡ ያለማቋረጥ በማስገኘት፡ እጆቿን ወደእግዚአብሔር ዘርግታ በምትኖረው ኢትዮጵያዊት ድንግል ማርያም ላይ የተፈጸመውና የሚፈጸመው፡ ይህን የመሰለውና ሌላውም፡ ማናቸውም ዓይነት፡ ሰብአዊም ኾነ ሰይጣናዊ ደባ፡ ከወዲሁ፡ በእውነተኛ ንስሓና ምግባር፡ ስሕተቱ ሊስተካከል፥ ጥፋቱም ሊወገድ ይገባል።

አለዚያ፡ ይኸው፡ በኢትዮጵያዊት ድንግል ማርያም ላይ የተፈጸመውና የሚፈጸመው፡ ይህን የመሰለውና ሌላውም፡ ማናቸውም ዓይነት፡ ሰብአዊም ኾነ ሰይጣናዊ ደባ፡ በእውነተኛ ንስሓና ምግባር፡ ስሕተቱ ካልተስተካከለና ጥፋቱ ካልተወገደ በቀር፡ በመንፈስ ቅዱስ ላይ እንደተሠነዘረ ስድብ ተቆጥሮ፡ "**በዚህ ዓለም ቢኾን፥ ወይም፡ በሚመጣው ዓለም፡ ለማይሰረይ ኃጢአትና ለዘለዓለማዊ ፍዳ የሚዳርግ መኾኑ፡**" በፍጥነት መታወቅ ይኖርበታል።

እግዚአብሔር፡ እንደቃል ኪዳኑ፡ ቀድሞ፡ በጥንተ ተፈጥሮ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልብ ላይ ጽፎትና በየልቦናቸው ውስጥ አሳድሮት፥ ኋላ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት በተገኘው፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋና በረከት፡ እንደገና አጽድቆትና አጽንቶት፡ በበለጠ እንዲያበራና እንዲያፈራ ካደረገው፡ <u>የሕጉና የሥርዓቱ እውቀት ጋር የማይስማማ፡</u> በልሳን ተያይዞ የተላለፈና በጽሑፍ ተከትቦ የተመዘገበ፡ ሰዎች በተቀበሏቸው፡ "ቅዱሳት" በተባሉት መጻሕፍት ውስጥ ጭምር ያለው፡ ማናቸውም ዓይነት ቃልና ነገር፥ ንግግርና መልእክት፥ ይትበሃልና ዘይቤ፥ ፍችና ትርጓሜ፥ ትችና ሓተታ ኹሉ፡ <u>ፍርስ፥ ውድቅ መኾኑ፡</u> ከእግዚአብሔር እውነታዎች አንዱ ነው። (ዘፍጥ. ፩፥ ፳፮-፳፯፤ ፪፥ ፯፤ ፫፥ ፳፪። ኤር. ፴፩፥ ፴፩-፴፬። ዮሓ. ፯፥ ፵፫። የሓዋ. ፪፥ ፩-፬። ዕብ. ፰፥ ፰-፲፪።)

ስለዚህ፡ ኾን ተብለው፡ በረቂቅ ተንኰልና ጥናት የተፈጸሙት፥ እየተካኼዱም ያሉት፡ እነዚያ፡ ከላይ፡ ቀደም ብለው የተጠቀሱትና እነርሱን የመሰሉት፡ ለማይሠረየው ኃጢአት የሚዳርጉት ታላላቅ ጥፋቶች፡ በሃይማኖታዊ ንስሓና በምግባራዊ ርትዕ፡ ታርመውና ተስተካክለው፡ በይፋ እስኪገለጡ ድረስ፡ ይህ፡ አዲሱ መጽሓፍ ቅዱስ ኾነ፥ ሌሎቹ፡ የእርሱን ፈለግ ተከትለው የተተረጐሙት ዕትሞች ኹሉ፡ በእኛ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ፡ ተቀባይነት የሌላቸውና ልንገለገልባቸው የማይቻለን መኾናችንን እንደተገነዘባችሁት እናምናለን።

የሰው ዘር ኹሉ፡ በእግዚአብሔር መልክ በተፈጠረበት ሰውነቱና በቅዱሱ ኪዳን፡ ከፈጣሪው በተቀዳጀው ኢትዮጵያዊነቱ፥ እንዲሁም፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም በተወለደው፡ በእግዚአብሔር ልጅ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት፡ በፈሰሰለት፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ተጠቅሞ፡ የሚጠበቅበትን የንስሓና የታማኝነት ግዳጅ፡ በጊዜው እንዲፈጽም፡ ከማይቋረጠው የበኩላችን ጸሎት ጋር እናሳስባለን።

\+ \+ \+